


# ዘላቂ የአውሮፕላን ማረፍያ መሠረተ ንድፍ/ፕላን (SAMP) - NEPA የአካባቢ ግምገማ  በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች

## አጠቃላይ

### 1. ዘላቂ የአውሮፕላን ማረፊያ መሠረተ ንድፍ/ፕላን ምንድን ነው?

ቀጣይነት ያለው የአውሮፕላን ማረፊያ መሠረተ ንድፍ/ፕላን (SAMP) በሲያትል-ታኮማ ኣለም ዓቀፍ የአውሮፕላን ማረፊያ (SEA) የወደፊቱን የተተነበየ ፍላጎት ለማሟላት የለውጥ ንድፍ ነው። የአውሮፕላን ማረፊያ መሠረተ ንድፍ/ፕላን እ.ኤ.አ. በ 2018 ተጠናቅቋል ። በአለምአቀፍ የአየር መጓጓዣ ማህበር እንደተገለጸው ፣ 56 ሚሊዮን አመታዊ መንገደኞችን እንዲሁም የበረራ እና የጭነት እንቅስቃሴን ለማገልገል የታቀዱ 31 የቅርብ ጊዜ ንድፎች/ፕሮጀክቶች (NTPs) ተለይቷል (IATA)።

በአሁኑ ወቅት የብሔራዊ የአካባቢ ጥበቃ ደንብ/ፖሊሲ (NEPA) የአካባቢ ጥበቃ ግምገማ በመካሄድ ላይ ነው, የ NEPA ረቂቅ ሰነድ በበልግ 2024 ይወጣል ተብሎ ይጠበቃል. የ NEPA ሂደቱ እንደተጠናቀቀ፤ የግዛቱ የአካባቢ ጥበቃ ደንብ/ፖሊሲ (SEPA) ግምገማ ይከተላል።

### 2. የቀረበው ንድፍ/ፕሮጀክት ሃሳብ ምንድ ነው?

የNTPs ዋና ዋና ቁልፍ ሃሳቦች(ማለትም, የግብይት ተግባር) ከእነዚህም መካከል ጎላ ያሉ ነጥቦች የሚከተሉት ናቸው፡- ሁለተኛ ተርሚናል ግንባታ፣ ማዕከላዊ ጥገና ምድረ ግቢ፣ ከአውሮፕላን ማረፊያ ውጪ ያሉ የጭነት ማጓጓዣ ቦታዎች፣ የአውሮፕላን ማረፊያ መንገዶች እንደገና እንዲገጣጠሙ ማድረግና የነዳጅ ማምረቻ ዎች መስፋፋት ይገኙበታል።

- ሁለተኛ ተርሚናል 19 ተጨማሪ በሮች  የአውቶቡስ መንገድ እና ጣቢያዎች
- አሁን ያለውን የኪራይ መኪና ተቋም፣ አዲስ ተርሚናል እና ዋና ተርሚናልን የሚያገናኝ ከፍ ያለ የአውቶቡስ መንገድ እና ጣቢያዎች
- የአሁኑን መገልገያዎች ለመተካት እና የአየር ማጓጓዣን ለማስተናገድ የጭነት መገልገያዎች
- የአውሮፕላን ማረፊያ መንገዶችን ማደስ
- የአየር ማረፊያ ማሻሻያዎች የደህንነት እና ውጤታማነት ለማሻሻል
- ሁለተኛውን ተርሚናል ለማገልገል አዲስ የመኪና ማቆሚያ መሠረተ ልማት
- ለዘላቂ የአውሮፕላን ነዳጅ ተጨማሪ ተቋማት

### 3. ለምን የኣይሮፕላን ማረፍያ ማስፋፋት አስፈለገ?

በ2021 በፐዩጅት ሳውንድ አካባቢ ምክር ቤት የተካሄደ አንድ የአካባቢ ያየር ማመላለሻ ጥናት እንዳሳየው፣ በተተነበየው ፍላጎት መሰረት በየዓመቱ 27 ሚሊዮን የሚሳፈሩ መንገደኞች እንዳሉ እና በ2050 ሲይትል optimal level of service በተመቻቸ ደረጃ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችለው ይሆናል።
ለወደፊት ለታቀደው ፍላጎት አዲስ መገልገያዎች ከሌሉ በሲይትል የኣይሮፕላን ማረፍይ ዙርይ መጨናነቅ ይጨምራል ፣ ይህም ተጨማሪ መዘግየቶችን እና የከፋ የአገልግሎት ደረጃን ያስከትላል።

## አካባቢያዊ ግምገማ

### 1. አካባቢያዊ ግምገማ ዓላማ ምንድን ነው?

አካባቢያዊ ግምገማ ዓላማ የታቀደው ንድፍ/ፕሮጀክት ከመካሄዱ በፊት ሊያመጣ የሚችለውን የአካባቢ ተጽዕኖ ለመገምገም ነው። ዋና ዓላማዎች የሚከተሉትን ያካትታሉ፤

- በመረጃ ላይ የተመሰረተ ውሳኔ
- በውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ውስጥ ሙሉ ግልፅነት እና የህዝብ ተሳትፎ
- ህጎችን እና ደንቦችን ማክበር
- ተጽዕኖዎችን ማስወገድ፣ መቀነስ ወይም ማቃለል የሚቻልባቸው መንገዶች መፈለግ

## 2. በ NEPA እና SEPA መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?

የብሔራዊ የአካባቢ ጥበቃ ህግ ደንብ፣ ወይም NEPA፣ የፌደራል ድርጅቶች ውሳኔ ከማድረጋቸው በፊት ያቀረቧቸውን ተግባራቶች የአካባቢ ተፅእኖን እንዲገመግሙ እና ለህዝብ ግብአት እድሎችን እንዲሰጡ የሚፈልግ የፌዴራል ደንብ/ፖሊሲ ነው። የፌዴራል ያየር ማመላለሻ ጥናት አስተዳደር ህጋዊ የ NEPA መሪ ድርጅት ነው።

የግዛቱ አካባቢ ጥበቃ ደንብ/ፖሊሲ ህግ ወይም SEPA በግዛት ደረጃ ያሉ ድርጅቶች ተመሳሳይ ነገር እንዲያደርጉ ይጠይቃል። NEPA EAን ተከትሎ፣ ወደቡም የተለየ ጥናት/ድርጊት ኣካባቢይዊ ጥናት ግምገማ ያካሂዳል። የሲያትል ወደብ በግዝቱ ውስጥ ባለው ህግ የ SEPA መሪ ድርጅት ነው።

## 3. የአካባቢያዊ ግምገማ (EA) ምንድን ነው?

አንድ የአካባቢ ግምገማ (EA) የፌዴራል እርምጃ ከፍተኛ ተፅዕኖ ይኖረው እንደሆነ ለመወሰን ዝግጁ ነው። በግልጽ እና ቁርጥ ይለ የአካባቢያዊ ተጽዕኖ መግለጫ (EIS) የማያስፈልግ ማንኛውም እርምጃ አስተማማኝ ያልሆኑ ወይም መፍትሔ ያላገኙ የአካባቢ ጉዳዮች ያሉት ተፅእኖ ዎች, የ EA ማዘጋጀትን ይጠይቃል።

## 4. በEA ንድፍ ላይ እንዴት አስተያየት መስጠት እችላለሁ?

የ EA ንድፍ ላይ አስተያየት መስጠት ህዝብ በአካባቢያዊ የምርመራ ሂደት ውስጥ ለመሳተፍ እና ለውሳኔ አሰጣጥ ሂደት አስተዋፅኦ ለማድረግ ወሳኝ መንገድ ነው። ወደቡ በቀላሉ ሊደረስበት የሚችል የሕዝብ አስተያየት ለመስጠት የሚቻልበትን መንገድ ለማዘጋጀት ቃል ገብቶኣል።
አንድ ጊዜ የህዝብ አስተያየት የሚሰጥበት ጊዜ በ2024 መገባደጃ ላይ ከተከፈተ የማህበረሰቡ አባላት እና ሌሎች ፍላጎት ያላቸው ወገኖች ወደ ስድስት ቋንቋዎች የተተረጎሙ መረጃዎችን መከለስ እና በአስተያየቱ ጊዜ ውስጥ አስተያየቶችን በህዝባዊ ስብሰባ፣ በመስመር ላይ፣ በኢሜል ወይም በመደበኛ ፖስታ ማቅረብ ይችላሉ። ሰነዱ በድረ-ገጻችን ላይ ይገኛል እና በBurien, Des Moines, Federal Way, SeaTac እና ሌሎችም ባሉ የህዝብ ቤተ-መጻሕፍት ይገኛል። አስተያየቶች ለድርጅቱ የአስተያየት ሰጪውን አቋም እና የተነሱት ጉዳዮች ለምን ለውሳኔ አሰጣጡ ጠቃሚ እንደሆኑ እንዲገነዘብ በቂ ዝርዝር መረጃ ማቅረብ አለባቸው።

## 5. የሕዝብ አስተያየት ጊዜ ምን ያህል ይሆናል?

FAA የ45-ቀን የአስተያየት ጊዜን አረጋግጧል፣ይህም ለNEPA EA መደበኛ የ30-ቀን የህዝብ አስተያየት ጊዜ ማራዘሚያ ነው።

## 6. አስተያየቴን ከሰጠሁ በኋላ ምን ይሆናል?

በአስተያየቱ ጊዜ ማጠቃለያ ላይ ሁሉም የተቀበሉት አስተያየቶች በFAA እና ወደብ የመጨረሻውን EA በሚዘጋጅበት ጊዜ ይገመገማሉ እና ግምት ውስጥ ይገባሉ። ለአስተያየቶች የሚሰጡ ምላሾች በመጨረሻው EA ውስጥ ይካተታሉ።

## 7. በዚህ የበአካባቢያዊ ግምገማ ሂደት ኣካሔድ ውስጥ ማህበረሰቦችን በእንዴት ሁኔታ እያሳተፋችሁ ነው?

የህዝብ ተሳትፎ ጥረት ግልፅነትን፣አካታችነትን እና ትርጉም ያለው ተሳትፎን ለማረጋገጥ በርካታ ቁልፍ ስልቶችን ያካትታል። እነዚህም ህዝባዊ ስብሰባዎች፣ የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ፣ ክፍት የአስተያየት ጊዜዎች፣ እና በዋና ዋና የንድፍ/ፕሮጀክት ምእራፎች ላይ የትርጉም እና ተደራሽነትን ያካትታሉ። አንድ ጊዜ የሕዝብ አስተያየት መስጫ ጊዜ በኦክቶበር 21፣ 2024 ከተከፈተ፣ የህብረተሰቡ አባላት ወደ ስድስት ቋንቋዎች የተተረጎመ መረጃን ገምግመው ማቅረብ ይችላሉ።
በህዝባዊ ስብሰባ ፣ በመስመር ላይ ፣ በኢሜል ወይም በመደበኛ ፖስታ በአስተያየቱ በሚከፈትበት ጊዜ ውስጥ አስተያየቶች መስጠት ይቻላል። ሰነዱ በድረ-ገጻችን ላይ ይገኛል እና በBurien, Des Moines, Federal Way, SeaTac እና ሌሎችም ባሉ የህዝብ ቤተ-መጻሕፍት ይገኛል።

## 8. እንዴት ተጨማሪ ማወቅ እና በ SAMP አካባቢያዊ ግምገማ ኣካሄድ ሂደት ላይ ማሻሻያ ማድረግ እችላለሁ?

የበለጠ ለማወቅ የንድፉ/ፕሮጀክታችንን ድረ-ገጽ በwww.sampntpenvironmentalreview.org ይጎብኙ።
በተጨማሪም በ "አካባቢ እና ዘላቂነት ዜና" ክፍል ስር ያለውን የአውሮፕላን ማረፊያ መሠረተ ንድፍ/ፕላን ማሳወቂያዎች ሳጥን በመምረጥ በ SAMP የቅርብ ጊዜ እቅድ/ፕሮጀክቶች አካባቢያዊ ግምገማ ውስጥ ለመቆየት ኢሜይሎችን ለመቀበል ደንበኛ ለመሆን መመዝገብ ይችላሉ።